# ማስታወቂያ

## <u>ለኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን</u>

ዳያስፖራው በግልና በማህበር ተደራጅቶ በሀገር ቤት የመኖሪያ ቤት ስለሚያገኙበት ሁኔታ  በጥናት ላይ የተመረኮዘ አሰራር እንዲሚዘረጋ በዳያስፖራ ፖሊሲ አንቀጽ 6.5 (2) በተደነገገው መሰረት መንግስት የቤቶች ልማት ፕሮግራም ዘርግቶ እንቅስቃሴ መጀመሩ ይታወቃል፡፡

በዚህ መሰረት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የግል፣ የአፓርትመንት እና የመኖሪያ ቤት ስራ ማህበራት የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች የማስፈፀሚያ መመሪያ በመንግስት እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡ መመሪያው ሲጠናቀቅ በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ ሀገር ያለውን ዲያስፓራ ምዝገባው በተቀናጀና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ማድረግ በማስፈለጉ በሀገር ቤት እየተከናወነ የሚገኘው የዲያስፖራ ምዝገባ ቆሞ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በሚሲዮኖች አማካኝነት የሚደረገው ምዝገባ በተመሳሳይ የጊዜ ሰሌዳ ከጥቅምት 1/2006 እስከ ታህሳስ 30/2006 እንዲሆን ተወስኗል፡፡

በመሆኑም ዲያስፖራው ለዚህ ጉዳይ ውክልና መሰጠት እንደሌለበት እየገለፅን፣ በቀጣይ ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ምዝገባው የሚካሄድ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲ**
**ዋሽንግተን ዲሲ**